# አውደ ኢትዮጵያ

ሰኔ 1 2000 | የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲን ህጋዊ መንግሥትንና ፍትሃዊ ስርዓትን የመጠየቅ መብት አለው | እትም 8

# የአነድነት ለዲሞክራሲና ለፍትሀ ፈጣንና ተሰፈ ሰጪ ጉዞ !

## ጠቅላላ ጉባዔውን ሰኔ ሰባት ያደርጋል

ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር በመሆን፣ ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ፣ በምርጫ ዘጠና ሰባት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ታይቶ የማይታወቅ ተዓምር የሰረ ድርጅት መሆኑ የሚረሳ ጉዳይ አይደለም። ይዞት የተነሳቸው አላማዎች የሰላም፤ የፍቅር፣ የአንድነትና የዲሞክራሲ ሲሆኑ፤ የኃይሉም መሰረት ከኢትዮጵያ ህዝብ የሚያገኘው ድጋፍ ብቻ ነበር። እንደ ገዢው የኢሕአዴግ ፓርቲ የጠመንጃ ኃይል ወይንም የኃያላን አገራት ድጋፍ አልነበረው። የመገናኛ ብዙሃንንም ሆነ ኢኮኖሚውን አይቆጣጠርም ነበር። በከባድ ሁኔታ ውስጥ እያለም የኢሕአዴግ አምባገነናዊ ሥርዓትን ለማነቃነቅ ብሎም ሥርአቱ ለብሶት የነበረውን የዲሞክራሲ ካባ ለመግፈፍ የበቃ ድርጅት ነበር።

ገዢዊ ፓርቲ በሰላማዊ ትግል የሚያምነውን ቅንጅት እንደ ጠላት ቆጥሮ ለማጥፋት በወሰነው መሰረት መሪዎቹን በግፍ ከ ሃያ ወራት በላይ ማሰሩ ይታወሳል። አቶ ስብሃት ነጋ አንድ ወቅት ባደረጉት ንግግር “ቅንጅት ጠላት ነው” በማለት በይፋ ማወጃቸውን ብዙዎች የሚያስታውሱት ነው።

ቅንጅት ከኢሕአዴግ ብቻ ሳይሆን በውሱጡም ከነበሩ አንዳንድ ኃይላት ጥቃት ደርሶበታል። አንዳንድ የአመራር አባላት ከድርጅቱ መርህና ሕገ ደንብ ውጭ በመንቀሳቀሳቸው አላስፈላጊ ውዝግብ ውስጥ ድርጅቱን መክተታቸው፣ አብዛኛውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሳዘነ ጉዳይ ነው። በቅንጅት አመራር አባላት መካከል የተፈጠረው አሳዛኝ ችግር ቅንጅትን ሊያጠፋውና ሊገድለው እንደሚችል ብዙዎች ሰግተው ነበር። አፍቃሪ ኢሕአዴግ ድህረ ገጾችም እየደጋገሙ የቅንጅትን ግባተ መሬት ሰያውጁ ከርመዋል።

የቅንጅቱ ሊቀመንበር በውጭ አገር ስለነበሩ፣ ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበሯ፣ ወይዘሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ፣ በአገር ቤት ያሉትን የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት አመራር አባላት በማሰባሰብና በማደራጀት፣ ይህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተስፋ የነበረውን ድርጅት እንደገና እንዲያሰራራ ለማድረግ ችለዋል። ላእላይ ምክር ቤቱ የጎደሉ አመራር አባላትን በመተካት፣ ቢሮ ተከራይቶ እንቅስቃሴውን ቀጥሉዋል።

ገዢው ፓርቲ የሚቆጣጠረው ምርጫ ቦርድ ፣ሕገ ወጥ በሆነ መልኩ የቅንጅትን ስም በአቶ አየለ ጫሚሶ ለሚመራው ቡድን ቢሰጥም፣ ቅንጅት መንፈስ እንጂ ስም ብቻ የቀድሞ የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት፣ አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ በሚል ስም እንቅስቃሴ ተጀመረ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ጉዳዩ ከስሙ ሳይሆን ጉዳዩ ቅንጅት አንግቦት ከተነሳው አላማ በመሆኑ ማን ምን እንደሆነ መለየት አላስቸገረውም።

ይህንን አዲስ ስም በሕግ ለማስመዝገብ ከአራት ክልሎች ከ 15000 በላይ የሚሆን ፊርማ፣ የፓርቲው የፖለቲካ ፕሮግራምና ደንብ እንዲሁም የመስራች ጠቅላላ ጉባዔውን ቃለ ጉባዔና የአመራር አባላትን ስም ዝርዝር መቅረብ አለባቸው። በዚህ መሰረት ከሰባት ክልሎች ከ 7000 ሺህ በላይ ፊርማ የተሰበሰበ ሲሆን የቀድሞ የቅንጅት ፓርቲ ፖለቲካ ፕሮግራምና ሕገ ደንብን በብዙ ባልቀየረ መልኩ ሰነዶች ተዘጋጅተው ተጠናቀዋል።

| | |
|---|---|
| አዲስ አበባ - አሥሩ ክፍለ ከተማዎችና ወረዳዎች | 99 |
| አማራዉ ክልል - አርባ ወረዳዎች | 66 |
| ደቡብ ክልል - ሰላሳ ሁለት ወረዳዎች | 60 |
| ኦሮሞያ ክልል - 37 ወረዳዎች | 57 |
| አፋር ክልል | 3 |
| ሶማሌ ክልል | 2 |
| ሃረሬ ክልል | 1 |
| የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት አባላት | 36 |
| የፓርላማ አባላት | 26 |

የቀድሞ ቅንጅት የአሁን አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ፣ ሰኔ ሰባት 2000 ዓ፣ም በኢምፔሪያል ሆቴል መሥራች ታሪካዊ ጠቅላላ ጉባዔውን ለማካሄድ የሚያስፈልገው ዝግጅት የተጠናቀቀ ሲሆን፤ በዚሁ ስብሰባ ከሰባት ክልሎች ተመርጠው የሚመጡ ተሳታፊዎች ሲኖሩ ሁሉንም ክልል ወክለው 54 ሴቶች  አባላት ይገኙበታል። የተወካዮች ብዛትና ክልላቸው በሰንጠረዡ ተዘርዝሯል።

በጉባዬው፣ የተዘጋጁት ሰነዶች (የፓርቲው ፖለቲካ ፕሮግራምና ሕገ ደንብ ) ውይይት ተደርጎባቸው ይጸድቃሉ። በሚጸድቀው ሕገ ደንብ መሰረት ከ350 ተሳታፊዎች ውስጥ 60 የላዕላይ ምክር ቤት አባላትና 15 ተጣባባቂ የላዕላይ ምክር ቤት አባላት ይመረጣሉ። ከስልሳ የላዕላይ ምክር ቤት አባላት ሊቀመንበር፣ አራት ምክትል ሊቀመናብርት ፣ አንድ ዋና ጸሃፊና አሥራ ሁለት የሥራ አስፈጻሚ አባላትን የያዛ የሥራ አስፈጻሚ አካል ይመረጣል።

ይህንን ታሪካዊ ስበሰባ እንዲሳተፉ ከመቶ በላይ ታዋቂ ግለሰቦች፣ ወጣቶችና፣ ከውጭ አገር የሚመጡ የድጋፍ ማህበራት ተወካዮች ተጋብዘዋል። ስበሰባው አንድ ቀን የሚፈጅ ስብሰባ ሲሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ በግልጽ ሊከታተለው እንዲችል ክፍትና ግልጽ ስብሰባ ነው የሚሆነው።

የቅንጅትን መንፈስ ይዞ የሚንቀሳቀሰው አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ጠቅላላ ጉባዔውን እንዳጠናቀቀ የ 1500 ዜጎችን ፊርማ ፣ የፓርቲውን ፕሮግራምና ህገ ደንድ፣ የጥቅላላ ጉባዔውን ቃላ ጉባዔና የተመራጭ አባላት ስም ዝርዝርን ለምርጫ ቦርድ ያቀርባል።

አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ በሕጉ መሰረት ለምርጫ ቦርድ ማመልከቻ ካገባበት ጊዜ ጀምሮ እንደ ፖለቲካ ፓርቲ በኢትዮጵያ ውስጥ መንቀሳቀስ ይችላል።

# የኢትዮ-ሱዳን ድንበር ጉዳይ - ከሕግ አንጻር

## ከዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማሪያም ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ

ዶ/ር ያዕቆብ ሃይለማሪያም ኢትዮጵያ ካፈራቻቸው እውቅ የሕግ ባለሞያ መካከል አንዱ ናቸው። ለበርካታ አመታት ቨርጂኒያ በሚገኝ ዩኒቨርስቲ የሕግ መምህር ሆነው የሰሩ ሲሆን፣ በተባበሩት መንግስታ የአለም አቀፍ ፍርድ ቤት አቃቢ ሕግ ሆነው በሩዋንዳ ጉዳይ ላይ አገልግለዋል። በናይጄሪያና በካሜሩን መካከል በተደረገው የድንበር ማዋሰን ሂደት ላይ የሕግ አማካሪመ ነበሩ። በአሁኑ ወቅት አገራቸውንና ሕዝባቸውን ለማገልገል በኢትዮጵያ ከሚውዱት ሕዝብ ጋር ይገኛሉ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለነጻነቱና ለመብቱ በሚያደርገው ትግል፣ በምርጨ ዘጠና ሰባት ወቅት ፣ በቅንጅት ሥር በመደራጀት ታሪካዊ ውጤት ማስመዝገቡ የሚታወስ ነው። ኢሕአዴግ የሕዝብን ድምጽ ለመቀልበስና በሥልጣን ላይ ለመቆየት በሰነዘረው የግፍ በትር  በርካታ ኢትዮጵያውያን ሞተዋል። በአሥር ሺህ የሚቆጠሩ ሲሰደዱ፣ የቅንጅት ከፍተኛ አመራር አባላትንም ጨምሮ በመቶ ሺህ ታስረዋል። ከታሰሩት የቅንጅት አመራር አባላት መካከል ዶ/ር ያዕቆብ ወልደማሪያም አንዱ ነበሩ።

እሥርና እንግልት ቢደርስባቸውም አሁንም ትግሉን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ለማድረግ ሕዝባቸውን ተቀላቅለው አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ የሚልን ስም በያዘው የቀድሞ ቅንጅት አመራር አባል ሆነው በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ።

ኢሕአዴግ ሕዝብን ሳያማክር በድብቅ ለሱዳን ስለሰጠው መሬት በተመለከተ የአንድነት ድምጽ ሬዲዮ አዘጋጅ አቶ አለማየሁ አበበ ከሕግ አንጻር ማብራሪያ እንዲሰጡ ዶ/ር ያዕቆብን እሑድ ግንቦት ሰላሳ 2000 ዓ.መ አነጋግሮ ነበር። ቃለ መጠይቁን በከፊል አቅርበንላቹሃለ።

**አንድነት ሬዲዮ - በዛሬው እለት ለአንድነት ድምጽ ስለቀረቡ በሬዲዮ አዘጋጆችና በዚህ አካባቢ ነዋሪዎች ስም በጣም አድርጌ አመሰግናለሁ።እንግዲህ ዛሬ በርግጥ በኢትዮጵያና በሱዳን ድንበር አካባቢ በተፈጠረው ችግር ብዙ ነገሮች ተብለዋል። የምሁራንም ጽሁፎች አንብበናል። በዚያ አካባቢ ያሉ ነዋሪዎችም የሚሉትን ሰምተናል። እርሶን ዛሬ ያቀረብነው በህግ አካባቢ ያለውን ሆኔታ ለህብረተሰቡ እንዲገልጹልንና እንዲያስረዱልን ስለፈለግን ነው። ይህም ማለት አንድ አገር እንዲህ አይነት የድንበር ማካለል በሚያደርግበት ጊዜ ምን ምን ማድረግ አለበት ? ለሕዝቡስ ለፓርላማውም በተለያየ መልክ ምንደነ ነው ማድረግ ያለበት? ይህንን ለመጠየቅ ነው።**

ዶ/ር ያቆብ - ከመነሻው ማንም ግለሰብ ይሁን አካል የኢትዮጵያን አንዲት  ጋት መሬት እንኳን አሳልፎ ለማንም መስጠት የሚያስችል ስልጣን የለውም። በህገ መንግስቱም እንዲህ አይነት ሥልጣን የተሰጠው አካል የለም። እንደውም የኢትዮጵያን አካል ገንጥሎ ወይንም ቆርሶ ለሌላ መስጠት በማንም በሥራ አስፈጻሚው አካል ይሁን በግለሰብ እንደውም በከፍተኛ ወንጀል የሚፈረጅ ድርጊት ነው። ነገሩ በከፋም ጊዜ ሞትም ድረስ እስከማስቀጣት ሊደርስ ይችላል። የወንጀል ህግ አንቀጽ 241 ይህንኑ ያረጋግጣል። የኢትዮጵያን ግዛት ወይንም ሕዝብ ከፊሎ የሚሰጥ ወይንም የመስጠት ተግባርን የፈጸመ አካል እስከ ሞት በሚያደርስ ቅጣት ሊቀጣ ይችላል። መሬት ቆርሶ ለሌላ አካል ወይንም ለሌላ አገር የመስጠት ሥልጣን ያለው የለም፡

በሌሎች ህዝብ አገሮች እንደተደረገው ኢትዮጵያ አሁን ከኤርትራ ጋር እንዳደረገችው ምናልባት በአንዳንድ ውሎች መሰረት (በኤርትራ በኩል የነበረው በርግጥ ስህተት ነው። ታሪካዊ ስህተት ነው) ድርድር ያደርጋሉ። በድርድሩ ምናልባት ባይሳማሙ እስከ ኢንተርናሽናል ኮርት ኦፍ ጀስቲስ ይሄዳሉ። ወይንም ደግም ኢትዮጵያና ኤርትራ እንዳደረጉት የግልግል ኮሚሽን አቋቁመው ሁኔታቸው በዚያ ይወሰናል። እንጂ የሥራ አስፈጻሚው አካል በተናጥል እራሱን ከአገሪቱ ቆርሶ  ለሌላ አገር የሚሰጠበት ሆኔታ በፍጹም የለም። በታሪክም እስከዛሬም የታየ አይመስለኝም።

አሁን በሱዳንና በኢትዮጵያ መሃከል ያለውን ወሰን በአንድ በኩል መሬት ወደ ሱዳን እንደሄድ በተለያዩ ሁኔታዎች ተረጋግጧል። ወንድሜ እንደገለጽከው ኢንቨስተሮች ተፈናቅለዋል። በአካባቢው ይኖሩ የነበሩ ሰዎችም ተፈናቅልዋል። ይሄ ሊደረግ የተቻለው በሁለቱ አገሮች መካከል በ1902 ተፈራርመዋል በተባለው መሰረት ነው። ነገር ግን ያም ስምምነት ቢሆን ከዚያ በኋላ በተደረጉ የደብዳቤ ልውውጥ ስምምነቶች ተሰርዟል የሚል ነገር አለ። እርሱም ቢሆን አገሮች ተደራድረው፣ የድርድሩ ውጤት ፓርላማ  ሄዶ ሲጸድቅ ወይንም ደግሞ በህዝበ ውሳኔ ሲጸድቅ እንጂ እንደዚህ በተናጥል የሥራ አስፈጻሚው አካል መሬት አንስቶ ለሌላው የሚሰጠበት ሆነታ በፍጹም የለም።

እና በዚህ በወሰን ማካለል ጉዳይ ላይ ብዙ ስህተቶች እየተፈጸሙ ነው ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው። በኤርትራ የሆነው ያው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ታሪካዊ ስህተት ነው የተፈጸመው። በወሰን አያያዝ ጉዳይ ላይ ኢሕአዴግ የሚወሰደው መስመር በፍጹም ትክክል አይደለም። ኢትዮጵያን የሚጎዳ ነው። አሁን በሱዳን በኩል ይሄ ተፈጽሟል።በሶማሊያም በኩል አንዳንድ ችግሮች አሉ። የርሱም ሁኔታ የተለየ ችግር ሊፈጥር ይችላል። እና የኢሕአዴግ አካሄድ ሕግ የተከተለ አይደለም። ሕገ መንግስቱንም እንኳን የተከተላ አይደለም።የራሳቸውን ሕገ መንግስት የተከተለ ሂደት እንኳን አይደለም።

አሁን ኢሕአዴግ መሬት ቢያስረክብ ይሄ የመጨረሻው ነው ማለት አይቻልም።

ወደ ገጸ 4 ዞሯል







የኢትዮጵያ መሬት ለሱዳን መስጠትን በተመለካተ ተቃዉሞ ሰልፍ በአለም ዙሪያ  ቀጥሏል። የዋሽንገተን፤ የጄኔቫና የፍራንክፈርት ሰልፍ (ፍቶ አባይና ዐቡጊዳ ሚዲያ)

# በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሽብሬዎች አሉ !

በኢትዮጵያ ምናልባትም በአለም ታሪካ የመጀመሪያ የሆነ፣ የምዕራባዉያን ዲፕሎማቶችን፣ ገዢዉን ፓርቲ እንዲሁም



የተቃዋሚ መሪዎችን ሁሉ ሳይቀር ያስደነገጠና ያስገረመ፣ ሕዝባዊ ትሱናሜ ተብሎ የሚታወቀዉ ሰልፍ ነዉ ሚያዚያ 29 ቀን 1997 በአዲስ አበባ ከተማ የታየዉ። ይህ ከአራት ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያዊ የተገኙበት ሰልፍ ካስተማረን አንዱና ዋነኛዉ ትምህርት፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጨዋነት ነዉ። በመስቀል አደባባይ ሕዝብ ከመሙላቱ የተነሳ እስከ ከእሥራዔል ጋራዥ፣የቀድሞ የሕዝብ ደህንነት ቢሮ፣ ስፖርታ ኮሚሽን፣ ጋንዲ ሆሲታላና አራተኛ ክፍለጦር ድረስ በአምስቱም መገዶች ሕዝብ ተጠቅጥቆ ነበር።

በዚህ ሰልፍ የአንድም ሰዉ ሕየወት ካለማጥፋቱ በተጨማሪ በፖሊስ የተዘገበ ረብሻም ሆነ አለመረጋጋት አልታየም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ህግ አስከባሪ ፖሊስ ባይኖርም ተከባብሮ ተዋዶና ተረዳድቶ የሚኖር ሕዝብ እንደሆነ ነዉ ቅንጅት የጠራዉ ሰላማዊ ሰልፍ ያሳየዉ።

ይህ ታላቅ ፣ ታሪካዊዉና አኩሪዉ ሰላማዊ ሰልፍ በተደረገ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ነዉ እንግዲህ አሳፋሪ፣ አሳዛኝና ጭካኔ የተሞላበት ድርጊት በምድራችን የተከሰተዉ። ገዢዉ ፓርቲ የሕዝብ ድምጽ ተቀጥሮ ሳያልቅ አሸንፌያለሁ ብሎ አወጀ። የዉጭ አገር ታዛቢዎች በሌሉበት ቦታ ኮረጆዎችን ቀየረ። በግልጽና በገሃድ የሕዝብን ድምጽ ሰረቀ።

እንደዚህም ሆኖ ሕዝቡ የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ አመራር አባላትን የሰላምና የመረጋጋት ጥሪ ስለተቀበለ የምርጫዉ ዉዝግብ ለመፍታት እየተደረገ ያለዉን ሰላማዊ ጥረት ተስፋ በማድረግ በትዕግስት ይጠባበቅ ጀመር።

ይህ ሕዝባዊ ጨዋነት ለገዢዉ ፓርቲ አልተመቸዉም። በምርጫ በትር ቢዘረርም የአጋዚ ጨካኝ ሰራዊቱን በአዲስ አበባ ከተማ አሰማርቶ ወታደራዊ ጡንቻዉን ለማሳየትና ሕዝቡ አንገቱን እንዲደፋ ለማድረግ አልተቻለዉም ነበር። ስለዚህ የአዲስ አበባ ዮኑቨርሲት ተማሪዎችን በመተንኮስ ቀዉስን መፍጠር እንደ አንድ አማራጭ አድርጎ ወሰደ። የደህንነት አባላትን በማሰማራት ተማሪዎችን ማንገላታት ጀመረ።

ተማሪዎችመ የተቃዉሞ ድምጻቸዉን አሰሙ። ከአዲስ አበባ ጊቢ ዉጭ ሳየወጡ፣ ድንጋይ ሳይወረዉሩና መስኮት ሳይሰብሩሕገ መንግስቱ የሚፈቅድላቸዉን ሰላማዊና ሕጋዊ ተቃዉሞ በካምፓሳቸዉ ዉስጥ ነበር ያደረጉት። ሰላምና እርቅን፣ ወንድማማችነትና ኢትዮጵያዊነት የሚያጎላ ቃላት ያዘለን የቴዲ አፍሮን "ያስተሰርያል " ተብሎ የሚታወቀዉን ጣዕመ ዜማ ያሰሙ ነበር።

የአጋዚ ወታደሮች ጊቢዉን ሰብረዉ ገቡ። ተማሪዎችን በከባድ ጨነት በግፍ በወታደር መኪና ጨኗቸዉ። ሸዋሮቢት ወደ ሚገኝ ዕስር ቤት ተማሪዎችን ለማጎር ጉዞ ጀመሩ።

በዚህ አፈና የተበሳጨዉ የአዲስ አበባ ሕዝብ ተቃዉሞዉን ማሰማት ጀመረ። "ልጆቻችንን የት ነዉ የምትወስዷቸዉ ? ጥፋታቸዉ ምንድን ነዉ? " እያለ መጠየቅ ጀመረ። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን የያዘዉ የወታደር የጭነት መኪና በኮተቤ ሲያልፍ የኮተቤ የመምህራን ኮሌጅ ተማሪዎች ተቃዉሟቸዉን ለማሰማት ተነሱ። በዚያ አካባቢ የሚኖረዉም ሕዝብ መንገዱን ለተወሰነ ጊዜ ዘጋ። በዚህ ወቅት የአጋዚ ጦር በሰላማዊ ዜጎች ላይ ጥይት ማርከፍከፍ ጀመረ። በርካታ ንጹህ ኢትዮጵያዉያን ቆሰሉ። የአሥራ ስድስት አመት ወጣት፣ ሽብሬ ደሳለኝ፣ በጥይት ተመታ ወደቀች።

በነጋታዉ ሰኔ 9 ቀን የአዲስ አበባ ሕዝብ ሰላማዊ ተቃዉሞዉን በየቦታዉ አሰማ። የአጋዚ ወታደሮች ከረጅም ረቀት በሚያልም መሳሪይ ግንባር ላይ እየተኮሱ ንጹሃን ዜጎችን ከመግደል አልተቆጠቡም። የጥይት ሰለባ የሆኑት ቁጥራቸዉ አስር፤ ሃያ፣ ሰላሳ ...እያለ ማደግ ጀመረ። ከመርጫ ዘጠና ሰባት በፊት እናየዉ የነበረዉ መጠናኛ የዲሞክራሲ ጨራ ጨለመ። እራሱን እንደ ዴሞክራት እየቀጠረ የነበረዉ ኢሕአዴግ ለካ ዉስጡ ጭራቅ ኖሮ የዲሞክራሲ ማስኩ ተገፈፈ። አምባገነንና ከደርግ ያልተሻለ መሆኑን አሳየ።

እነዚህ በአጋዚ ጥይት የተገደሉ ወገኖቻችን፣ ሕገ መንግስቱ የሚፈቅድላቸዉን ሰላማዊ ተቃዉሞ ማሰማታቸዉ ነዉ እንግዲህ እንደ ወንጀል ተቆጥሮ ያስገደላቸዉ።

"የአዲስ አበባ ቦዘኔዎችን፣ አስተባብሮ፣ በኃይል መንግስትን ለመገልበጥ፣ ቅንጅት ያደረገዉን ሙከራ ለማክሸፍ ነዉ ወታደር ያሰማረሁት " በማለት ነበር እኩይ ሥራዉን ለማስተባበል የሞከረዉ።

የአዲስ አበባ ነዋሪ ግን ጨዋነቱን በሚያዚያ 29 1997 በገሃድ አሳይቷል። በሰለጠነ ፖለቲካ የሚያምን ጨዋ ሕዝብ እንደሆነ ገዢዉ ፓርቲ እራሱ ያዉቀዋል። ኢትዮጵያዉያን የጠየቁት መብታቸዉንና ነጻነታቸዉን ነዉ። ለመብታቸዉ፣ ለነጻነታቸዉ፣ ለኢትዮጵያ ክብርና አንድነት ኢትዮጵያዉያን በሰኔ 1 እና ሰኔ 2 የሕወሃት/ ኢሕአዴግ የግፍ በትር አረፈባቸዉ።

ገዢዎ ፓርቲ በጠመንጃ ኃይል፣ የሕዝብን ድምጽ ሰርቆ አሁንም በሥልጣን ላይ ይገኛል። "ይህን ሕዝብ አርፎ እንዲቀመጥ አድርገነዋል" ብሎ ሊዝናና ይችላል። ነገር ግን እነ ሽብሬ ደሳለኝ የተሰዉለት ትግል ከመቼዉም በበለጠ እየተቀጣጠለ ነዉ። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሽብሬ ደሳለኞች ተወልደዋል። በአዲስ አበባ፣ በጎንደር፣ በመቀሌ፣ በጅጅጋ፣ በቡታጅራ፣ በአምቦ፣ በነጆ፣ በአሳይታ ...የዲሞክራሲ ደዉል እየተሰማ ነዉ። በዉጭ አገር የሚኖረዉም ኢትዮጵያዊ ከመቼዉም በበለጠ ተንቀሳቅሷል።

እነ ሽብሬ ደሳለኝ አስክሬናቸዉ ከመሬት በታች ቢሆንም አሁንም ድምጻቸዉ ከተቀበሩበት ቦታ እየተሰማ ነዉ። "ነጻነት በነጻ የሚገኝ አይደለም። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ መነሳት አለበት። አለመሰዋዕትነት ድል የለም። እኛ ደማችንን ያፈሰስንበት፣ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲና የሕግ የበላይነት እንዲኖር የሚደረገዉ ሰላማዊዉን ትግል ከግቡ አድርሱት" ይሉናል።

ለዚህ ጥሪያቸዉም መልሳችን ግለጽና የማያሻማ ነዉ። "መሥዋእትነታችሁን በፍጹም አንረሳም። ትግሉን ከመቼዉም በበለጠ እናጠናክራለን። ዲሞራክራሲና የሕግ የበላይነት የሰፈነባት፣ ኢትዮጵያዉያን በኢትዮጵያዉያን እጅ በግፍ የማይገዳደሉባትና በዉስጧ ለሚኖሩ ልጆቿ ሁሉ እኩል የሆነች አንዲት ኢትዮጵያን እንገነባለን!" የሚል ነዉ መልስችን። ይህ ደግሞ በቃላትና በወሬ ብቻ ሳይሆን በተግባር የምናስመሰክረዉና የቆረጥንበት ጉዳይ ነዉ። ኢትዮጵያዉያን በአንድነትና በጋራ ከተነሳን መድረስ ከምንፈልገዉ ግብ የማንደርስበት አንዳች ምክንያት የለም።

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የኢትዮ-ሱዳን ድንበር…

ከገጽ 2 የዞረ

ምክንያቱም ሥልጣን የለውም። በፓርላማ የጸደቀ ጉዳይ አይደለም።ተተኪው መንግስት ይሄን ጉዳይ እንደገና ሊያነሳው ይችላል። መቼም ኢሕአዴግ ዘላለም በሥልጣን ላይ ይኖራል የሚል ግምት የሚኖር አይመስለኝም። ለተተኪ መንግስት በሚቀርብበት ጊዜ እነኚህ ጉዳዮች ሕግን ተከትለው፣ የኢትዮጵያን ሕገ መንግስት ተከትለው የተፈጸሙ ድርጊት ስላልሆነ በጊዜው ተነስቶ ሊሻር የሚቻልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል።

እንግዲህ በአብዛኛውን ሁሉም እንደሚያውቀው የኢንተርናሽናል ህግ ጉዳይ የጉልበት ጉዳይ ነው። እና የሚያሳዝነው አገራችን እየቀጨጨች በምትሄድበት ጊዜ ሱዳን ደግሞ እየበለጸገችና እየጎለበተች እየሄደች ነው። ምናልባት እነኚህ የተደረጉ ስምምነቶች ወይንም የተሰጠው መሬት የመጨረሻ ይሆናል ወይ የሚል ፍርሃትም ይኖራል በርግጥ። ግን አለም አቀፍን ሕግ በተመለከተ ግን ይህን ጉዳይ እንደገና ማስተካከል የሚኖርበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል ብዬ ግን አምናለሁ።

**አንድነት ሬዲዮ- እሺ በጣም አመሰግናለሁ። ባለፈው ሳምንት እንዲሁም በመተማና በታችኛው አርማጭሆ የፓርላማ ተመራጭ ተወካይ አቅርበን ይሄንን ጉዳይ ማለትም አቶ አስፋው ሰጠኝ ይባላሉ በ1997 ዓ.ም በምርጫው አሸንፈው አሁን ፓርላማ የሚገኙ ናቸው። ይሄን ጉዳይ ብታነሱ እግራቹህ ነው የሚቆረጠው እንዲሁም አፋችሁን በዚህ ጉዳይ ላይ መክፈትም አትችሉም የሚል ማስፈራሪያ ተሰቶናል ነው ያሉ እራሳቸው። ይህን ህግን ተከትሎ የሄደ ጉዳይ አይደለምና እንዲህ አይነት ሁኔታዎ ያለፈበት ሁኔታ ነው።ለምንድን ነዊ ዶ/ር ያዕቆብ መንግስት ይሄንን ጉዳይ በድብቅ ለማድረግ የፈለገው ብለው ያማናሉ ? ሕዝብ ተወያይቶበት ፣ ህዝብ አውቆት ፣ ማድረግ ያልተፈለገበት ምክንያት ምንድ ነው ?**

እንግዲህ ብዙ ምክንያቶች መዘርዘር ይቻላል። እኔ ምናልባት አንድ ማስበው ነገር ቢኖር የኢትዮጵያ ሕዝብ የወሰን ማካለለን ጉዳይ በጣም ከልቡ አጠገብ አድርጎ የሚያው ጉዳይ ነው። ለብዙ ዘማናት በታሪክ እንደሚታየው የኢትዮጵያ ወሰኖች በኢትዮጵያ ሕዝብ ደም የራሱ ናቸው። እነኝህ ወሰኖች በማይሆን መንገድ በሚጣሱበት ጊዜ ሕዝቡን በጣም የሚያስቆጣ ጉዳይ ነው። ስለዚህ ሕዝቡን በመፍራት ይመስለኛል ጉዳዩን በገሃድ እንዲወጣ ተደርጎና ሕዝቡ ተወያቶበት ለማካለል ያልፈለጉት። በዚሁ ምክንያት ይመስለኛል- የሕዝብን ቁጣ ያስከትላል በሚል።
ከዚህ በፊትም ተገልጿል። በአጼ ኃይለሥላሴ ዘመን እንደዚሁ ለሱዳን መሬት ተሰጥቷል የሚለው ዜና ተነስቶ ፓርላማ ውስጥ ከፍተኛ ረብሻ ተፈጠረ። ጎንደርም ውስጥ ከፍተኛ ረብሻ ተፈጥሮ ነበር። ምናልባት እንግዲህ ኢሕአዴግ ይሄንን በመፍራት ሳይሆን አይቀርም በሚስጥር ሊያካሂደው የፈለገው። እንግዲህ እኔ አንድ የሚያየኝ ምክንያት ይሄ ነው።

ሌሎች ሌሎችም ምክንያቶችም ሊኖሩ ይችላሉ። ምናልባት ስፔኩሌሽን ወይንም ግምት ስለሆነ መዘርዘሩ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል። ግን እኔ እንደሚመስለኝ በመሰረቱ ሕዝቡን በመፍራት ይመስለኛል። ቅድም እንዳልኩት የወሰን ጉዳይ ኢትዮጵያውይን ከልማቸው አጠገብ ያለ ነገር ነው። በኤርትራ ጉዳይ በተሰራው ምን ያህል ቁጣ እንዳስከተለ ሁላችንም የምናውቀው ነው። እስከዛሬ ድረስ ሕዝባችን የሚያንገበግበው ነው። ሁላችንምም የሚያንገበግብ ጉዳይ ነው። የያኔው ሁኔታ እንደገና እንዳይከሰት በሚል እንደው ነገሩን ሽፋፍኖ ለማለፍ የተደረገ ነገር ይመስለኛል።

**አንድነት ሬዲዮ - ኢትዮጵያ ውስጥ የህበረተሰቡ ስሜት ምን ይመስላል ?**

የሕበረተሰቡ ስሜት ከአንዳንድ ሰዎች ጋራ ስንገናኝ እንደዚሁም አንዳንዴ በጋዜጣ እየፈሩም እየቸሩም ቢሆን የቁጣ ቃላት ይገልጻሉ።በህዝቡ በኩል ከፍተኛ ቁጣ አለ ማለት ይቻላል። ይሄ የሚከተል ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ይሄ የተለመደ ነው፡ ወሰን በሚነካ ነገር የኢትዮጵያ ሕዝብ በጣም ይቆጫል። እና የኢትዮጵያን ወሰን ለማስከበር ዘመድ ወዳጁን ያላጣ ሰው የለም። የሁሉም ሰው ጉዳይ ነው። የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ጉዳይ ነው። በዚህ በኩል ከፍተኛ ቁጣ እንዳለ በርግጥ ይታያል። እናንተ ውጭ ባላችሁበት የነጻነት ድባብ ውስጥ አይደለም ያለነው፡፡ባልተስማማንበት ጊዜ ተነስተን ተቃውሞ ሰልፍ ማድረግ አንችልም። በዚህ ምክንያት ተቃውሞ የማድረግ መብት መታፈን ነው እንጂ እርግጠኛ ነኝ በዚህ ጉዳይ ከፍተኛ ሰልፍ ሊኖር ይችል ነበር። ግን በሕዝቡ በኩል ከፍተኛ ጉምጉምታ ከፍተኛ ቁጣ እንዳለ በግልጽ የሚታይ ጉዳይ ነው።

# ሚሊዮን ሽብሬዎች አሉ

ከገጽ 3 የዞረ

ካለሽበት ቦታ አድምጪኝ ሽብሬ
ገድል ጀግንነትሽን ይዥው እስከዛሬ
በዉጭ በአደባባይ በዉስጥ በሹክሹታ
እናወራዋለን ጠዋትና ማታ።

ሰፈር ምድሩ ሰላም ምስሎሽ ከቤት ወጣሽ
አገር በቀል ነቅዝ አጋዚ አገኘሽ
ወንድሞቻችንን አሥራችሁ በጭነት
በኮተቤ መንገድ ወደ ሸዋሮቢት
«ለምንድን ነዉ እኮ በግፍ
ምትወስዷቸዉ?»
ብለሽ ብትጠይቂ የእነርሱ መልሳቸዉ
ማነጋገር ሳይሆን እንደ ስልጡን ሰዉ
እንደ አዉሬ ደንብሮ ጥይት መርጨት ነዉ።

መሥሏቸዉ ይሆናል ጸጥ የሚያሰኙሽ
አልመዉ ተኩሰዉ ገድለዉ ቢጥሉሽ፤
አላወቁም እንጂ ደምሽን አፍሰሽ
መሬቱን አርጥበሽ ተዓምርን ሰራሽ።

የፈሰሰዉ ደምሽ ትልቅ ደዉል ሆኖ
የተኛዉን ሁሉ ከእንቅልፍ አብንኖ
ቀድሞ አንዲት ብቻ ሽብሬ ነበርሽ
አሁን በሚሊዮን ትቆጠሪያለሽ።

አሰላ ጅጅጋ አምባሰል ያቤሎ
ናዝሬት አሳይታ መቱ ደንቢዶሎ
አዲስ አባ ጅማ መቀሌ አሶሳ
ሃረር ድሬደዋ ወልቂጤ አዋሳ
በየብታዉ ሁሉ በዉጭ አገር ሳይቀር
ሽብሬዎች ሆኖ በሚሊዮን ሚቆጠር።

ጥያቄሽ መሻትሽ ደሞክራሲ ነበር
ሰላም መፈቃቀር እንዲበዛ በአገ፤
የኢትዮጵያ አንድነት የዜጎቿ መብት
ይከበር ስትይ አገኘሽ ጥይት።

ጥያቄሽ አይሞትም ይጧጧፋል እንጅ
ብዙ አሏት ኢትዮጵያ እንዳች ያል ልጅ
የአገር በቀል ነቀዝ ሆና መጫወቻ
አይፈቅዱም ልጇቿዉ እንድትሆን መዘበቻ።

አማኑኤል ዘሰላም



የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ በሰሜን አሜሪካ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች ማኅበር
766 Rock Creek Church Rd., NW .Washington DC, 20010 *ስልክ (202) 541-0556
ፋክስ: (202) 541-0557.*ኢሜል: kinijitna@kinijitna.org
Www.kinijitna.org

አስተያየቶን በ awdeethiopia@gmail.com ይጻፉልን